ወርኃዊ ጥንቅር ቁጥር 2
ሚያዚያ 2017 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፡- ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፡- ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፡- ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የአንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


መደበኛ ስብሰባዎች ........ 1

የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች ........ 2

የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ........ 8

የፓርላማ ዲፕሎማሲ ........ 11

የቋሚ ኮሚቴ አመራሮች ስየማ ........ 12

የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ ........ 13

ምክረ-ሐሳቦች ........ 18

ይኽ የሚያዚያ ወር የእንደራሴ ዕትም፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. እንደራሴዎች ካከናወኗቸው አበይት ተግባራት መካከል፣ የምክር ቤቱ ተልዕኮዎች የሆኑትን ሦስት ዋንኛ ጉዳዮችን አካቷል። እነዚህም፣ ሕግጋት ማውጣት፣ የአሥፈጻሚ አካላት ቁጥጥር እና የፓርላማ ዲፕሎማሲ ናቸው። የዚህ ወር ዕትማችን፣ እንደራሴዎቹ ያጸደቋቸውን ሕግጋት፣ የፈጸሟቸውን የእንደራሴነት የውክልና ተግባራት፣ ያደመጧቸውን የተቋማት ሪፖርቶች እና የከወኗቸውን የመስክ ጉብኝቶች፣ እንዲኹም የፈጸሟቸውን የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን አሰባስቦ እና በተመረጡት ኹለት አንኳር ጉዳዮች ላይ የብሪፎችን አጭር ዳሰሳዊ ምልከታዎችን አካቶ አቅርቧል።

# መደበኛ ስብሰባዎች

**ሚያዝያ 7**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 23ኛ መደበኛ ስብሰባ

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማድመጥ፤

**ሚያዝያ 7**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 24ኛ መደበኛ ስብሰባ

የትምህርት ሚኒስቴርን የ2017 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማድመጥ፤

**ሚያዝያ 8**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 25ኛ መደበኛ ስብሰባ

የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅን አስመልክቶ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ዐዋጁን ማጽደቅ፣ የተቀናጀ የውኃ ሀብት አሥተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ ዐዋጅን አስመልክቶ የውኃ፣ መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ዐዋጁን ማጽደቅ፤

**ሚያዝያ 20**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 26ኛ መደበኛ ስብሰባ

የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርን የ 2017 በጀት ዓመት የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ማድመጥ እና ውይይት ማድረግ፤

**ሚያዝያ 21**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 27ኛ መደበኛ ስብሰባ

የእንስሳት ጤና እና ደህንነት ረቂቅ ዐዋጅን አስመልክቶ የውኃ፣ መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ማጽደቅ፤

**ሚያዝያ 28**

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 28ኛ መደበኛ ስብሰባ

የገቢዎች ሚንስቴርን የ9 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማድመጥ እና መወያየት፤

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባሮች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በሚያዚያ ወር ሦስት ዐዋጆችን ያጸደቀ ሲሆን፤ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር የተላኩ ረቂቅ ዐዋጆችም ሆኑ በረቂቅ ዐዋጆች ላይ የተደረጉ አስረጂ መድረኮች በወሩ ውስጥ አልተካሄዱም።

## የጸደቁ ሕግጋት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በወርኃ ሚያዚያ ካፀደቃቸው ሕግጋት አንዱ፣ የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅ ነበር። በ25ኛው መደበኛ ስብሰባው፣ ምክር ቤቱ የቀረበለትን ይህንኑ ረቂቅ ዐዋጅ መርምሮ ዐዋጅ ቁጥር 1374/2017 በማድረግ፣ በ1 ተቃውሞ በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል። የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ ረቂቁን አስመልክቶ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል። የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌም የዐዋጁ፣ ጠንካራ ተቋምን ለመገንባት እና የዜጎችን እና የአገርን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰዋል። የ ባለፉት ሰባት አመታት 122 የነበሩት የሚዲያ ተቋማት፣ አሁን ወደ 272 ማደጋቸውን ያነሱት ተስፋዬ፣ 25 የነበሩት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች 7 103 ሲደርሱ፣ የሬዲዮ ጣቢያዎችም ከ52 ወደ 125 ከፍ ማለታቸውን አውስተዋል፤ ከዚህ ባለፈም፣ ሚዲያዎች የሚጠቀሟቸው ቋንቋዎች ከ29 ወደ 58 ከፍ ማለታቸውን ያነሱት ሚኒስትሩ፣ ለአብነት ይህ የተሻሻለው አዋጅ፣ ጠንካራ ሚዲያዎችን ለመገንባት አስፈላጊ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ዐዋጁ የበረቱ ትችቶችንም አስተናግዷል። (ስለ ተሻሻለው ዐዋጅ ዝርዝር ሃሳቦችን ጨምሮ፣ አጠር ያለውን የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ ገጽ 13 ላይ ይመልከቱ።)

በሚያዚያ ወር በኹለተኛነት የቀረበው፣ የተቀናጀ የውኃ ሀብት አሠተዳደር ማስፈጸሚያ የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ማቋቋሚያ ዐዋጅ ሲሆን፣ ረቂቅ ዐዋጁም በውኃ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ፈቲያ አህመድ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ቀርቦበት፣ ምክር ቤቱም በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል። ከዚህ ቀደም ብሎ፣ በረቂቅ አዋጁ የሚቋቋመው የተፋሰሶች ከፍተኛ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መዘጋጀቱ የውኃ ጉዳይ የሚፈልገውን ከፍተኛ ትኩረት የሚያመላክት ነው ሲሉ የተደመጡት ፈቲያ፣ ዐዋጁ ኢትዮጵያ ያላትን የገፀ-ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃን በፍትሓዊነት እና በዘላቂነት መጠቀም እንድትችል ያደርጋል ብለዋል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ በውኃ ጉዳይ ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በማቀናጀት ውጤታማ የውኃ ሀብት አስተዳደር እንዲኖር የሚያደርግ ነው ማለታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል። ከውኃ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ሳይንሳዊ መፍትሔ በመስጠት የላቀ አበርክቶ እንደሚኖረውም ተገልጿል። ዐዋጁም፣ ዐዋጅቁጥር 1375/2017 ተብሎ ሊጸድቅ ችሏል። እንደራሴዎቹ፣ በሦስተኛነት ሊያጸድቁት የሻቱት ረቂቅ ዐዋጅ፣ በግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ የቀረበበትን፣ የእንስሳት ጤና እና ደህንነት ዐዋጅን ነበር። ሰብሳቢው፣ በአገሪቱ እየተንሰራፋ የመጣውን ከሰው ወደ እንስሳ እና ከእንስሳ ወደ ሰው ተላለፊ የሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ያካተተ አዋጅ እንደሆነ፣ ባቀረቡት የውሳኔ ሐሳብ አንስተዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ወደ አገር የሚገቡትንም ሆነ ከአገር የሚወጡትን እንስሳት እና የእንስሳት ምርት የዓለም ዓቀፉን የእንስሳት ጤና ድርጅት አሰራር እና ሕግ በተከተለ መልኩ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ያሉት ስለሞን፣ ዘርፉ ለአገሪቱ ሊያበረክት የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያጎለብት እንደሆነም ተናግረዋል ተብሏል። ወቅቱን የጠበቀ ዓለም ዓቀፋዊ እና አህጉራዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን የዳሰሰ ነው የተባለው ይህ ረቂቅ ሕግም፣ ዐዋጅ ቁጥር 1376/2017 ሆኖ በሙሉ ድምጽ መጽደቁን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መረጃ ያመለክታል።

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ እንዲፈጽሟቸው ከሚጠበቁባቸው የእንደራሴነት ኀላፊነቶች ሌላኛው አሥፈጻሚ ተቋማትን መቆጣጠር ነው። በዚኽ ረገድም፣ የአሥፈጻሚ ተቋማትን ሪፖርት ማድመጥ፣ ተቋማቱን በአካል ተገኝቶ መገምገም እና የመስክ ጉብኝቶችን ማድረግ የሚጠቀሱት ክንዋኔዎች ናቸው።

## የአሥፈጻሚ ተቋማት ሪፖርቶች

በወርኃ ሚያዚያ፣ የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ለሚመለከቷቸው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከ 8-9 ወራት የሚደርስ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶቻቸውን አቅርበዋል። አስቀድሞሚያዚያ መግቢያ ላይ ሪፖርቱን ያቀረበው የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ሲሆን፣ የሚኒስቴሩን የ2017 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ያቀረቡት ክብርት ሚኒስትሯ ሙፈሪያት ካሚል ነበሩ። በዘጠኝ ወራት ውስጥ 3.4 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን በሪፖርታቸው ያነሱት ሚኒስትሯ፣ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት ዜጎችን በማሠልጠን በዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተሰራው ሥራ ውጤት ማምጣት መቻሉን ገልጸዋል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት አገራዊ ዕገድትን ለማፋጠን ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑንም ሙፈሪያት ተናግረዋል ተብሏል። የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ በበኩላቸው፣ ተቋሙ ለዜጎች የሥራ ዕድል ፈጣራ እንዲሁም ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሰራውን ሥራ በጥንካሬ አንስተው፣ የውጭ አገራት የሥራ ሥምሪት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ በይበልጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በቀጣይ ተኩረት የሚሹ ጉዳዮች መሆናቸውን አስገንዝበዋል። ከዚህ ባለፈም፣ የሥራና አሰሪ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በተያያዘ እያጋጠመ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባም ነገሪ ማሳሰባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።

በኹለተኛነት የ9 ወር ሪፖርቱን ያቀረበው ትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን፣ ሪፖርቱንም የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ አቅርበዋል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው፣ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት እየሰራ መሆኑን ካወሱበት ሪፖርት መካከል፣ የሚከተሉት ርዕሰ-ጉዳዮች አንኳር የሪፖርታቸው ነጥቦች ነበሩ፤

- በ 2017 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ከቅድመ አንደኛ እስከ ዐሥሥራ ኹለተኛ ክፍል 25 ሚሊዮን 253 ሺህ 365 ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እንደሚገኙ፤
- በጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት 1 ሚሊዮን 252 ሺህ 63 ሰዎች እየተከታተሉ መሆኑ፤
- በርቀት ትምህርት 71 ሺህ 445፣ በተፋጠነ ትምህርት 61ሺህ 251 እና በማታ ትምህርት 152 ሺህ 284 ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እንዳሉ፤



- በ2017 የትምህርት ዘመን ከቅድመ አንደኛ እስከ 8ኛ ክፍል 6 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተማሪዎችን የምገባ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፤
- በ1ኛ እና በ2ኛ ዙር  43 ነጥብ 5 ሚሊዮን የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሓፍት ስርጭት መከናወኑ፤
- ለ7 ሺህ 262 የትምህርት ቤት አመራሮች በልዩ የክረምት የትምህርት ቤት አመራር ሥልጠና መውሰዳቸው  እና ከነዚህ ውስጥ 6ሺህ 983 የሚሆኑት አመራሮች ምዘና እንዲወስዱ መደረጉ፤
- ለ43 ሺህ827 መምህራን በልዩ የክረምት ሥልጠና ሲወስዱ፣ ከነርሱም ውስጥ 61 ነጥብ 4% የሚሆኑት 70%  እና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገባቸው፤
- “ትምህርት ለትውልድ” በሚል መሪ ቃል በ2017 የትምህርት ዘመንብቻ 54 ቢሊዮን ብር ሲሰበሰብ፣  ከዚህ ሀብት ውስጥም 5 ሺህ 906 ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ 832 አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ፣ 712 ኹለተኛ ደረጃ፤ በድምሩ 6 ሺህ 815 አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸው፤
- 22 ሺህ 348 ለሚሆኑ ከቅድመ አንደኛ እስከ 2ኛ ደረጃ ያሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ እድሳት ሲደረግላቸው፣10 ነጥብ 187 ከቅድመ አንደኛ እስከ ኹለተኛ ደረጃ ላሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ተጨማሪ  የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ መከናወኑ፤
- በአገር አቀፍ ደረጃ በኢንስፔክሽን አገልግሎት ደረጃ ሦስት እና ከዛ በላይ ያገኙየአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ7 ነጥብ 8% ወደ 13 ነጥብ 2% ሲያድጉ፤ እየኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ ደግሞ ከ16 ነጥብ 21% ወደ  32 ነጥብ 69% መድረስ መቻላቸው፤
- 16 ሞዴል የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመገንባት ላይ ሲሆኑ፣ ተጨማሪ 15 ሞዴል የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ሥራ ለማስጀመር በሂደት ላይ እንደሚገኝ፤
- በ 2018 ዓ.ም. . የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚቀበሉ 5 ልዩ የኹለተኛደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤቶች  እየተገነቡ እንዳሉ፤
- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከተጎዱ ትምህርት ቤቶች መካከል በአማራ ክልል 45 እና በአፋር ክልል 4 ትምህርት ቤቶች  ተገንብተው መጠናቀቃቸው፤
- የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የማለፍ ምጣኔ መቀነስ ምክንያት ለማወቅ ጥናት በማጥናት፣ በግኝቱም መሠረት በ 2017 ዓ.ም.  የማለፍ ምጣኔን ለማሻሻል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ፤
- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የራስ ገዝነት ተሞክሮን በመቀመር 9 ዩኒቨርሲቲዎች ወደራስ ገዝነት ለመሸጋገር ወደሥሥራ መግባታቸው እና፤
- ከዚህ በጀት ዓመት ጀምሮ የኹሉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ማንኛውም ዓይነት ዲፕሎማ የሚታተመው በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ብቻ እንደሚሆን የሚሉት ይገኙበታል።

የፕሮፌሰሩን ሪፖርት ተከትሎም፣ የምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ የተጀመረው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ፣ የመምህርን እና የትምህርት አመራሮች ሥልጠና እንዲሁም የተማሪዎች ምገባ ወጥ በሆነ መልኩ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አስገንዝበዋል ተብሏል። የመምህራን እጥረትን ለማቃለል የተቋረጠውን የክረምት መርሃ ግብር ትምህርት ማስቀጠል አንዱ መፍትሄ ሊሆን እንደሚችልም የጠቆሙት ነገሪ፣ በተለያዩ የአገሪቱ አከባቢዎች በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ችግሮች ከትምህርት ገበታቸው ያቋረጡ ተማሪዎች መፍትሔ እንዲሰጣቸውም ለትምህርት ሚኒስትሩ አሳስበዋል ተብሏል።

በሦስተኛነት የክዋኔ ሪፖርቱን ያቀረበው የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ሲሆን፤ ሪፖርቱንም በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል።ቋሚ ኮሚቴውም፣ የባለሥልጣኑን የ2015/16 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መነሻ በማድረግ ውይይት ማደርጉን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ክብርት ዶ.ር. የሺ እመቤት ደምሴ፣ የመንግስት ግዥን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ ለመፈጸም የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ የሚያስፈልጉ የሕግ ማዕቀፎች ጸድቀው ወደ ስራ እንዲገቡ ሊሰራ እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል። የግዥ ሥርዓቱ እና የግዥ ትዕዛዝን በሚመለከትም ከፋይናንስ ተቋማት፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በትስስር መስራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል ያሉት የሺ እመቤት፣ ባለሥልጣኑ ልዩ ግዥዎች ወደ ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት የሚገቡበትን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ለኦዲት ምቹ እና በቂ መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ ይገባልም ብለዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አራሬ ሞሲሳ በበኩላቸው፣ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓቱን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ ባለሥልጣኑ ክፍተቶች በአሰራር እንዲስተካከሉ የሚያስችሉ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለክትትል እና ቁጥጥር ሥራው ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር እንደሚገባ መናገራቸው ተመላክቷል። የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥስልጣን ዋና ዳይሬክተር መሰረት መስቀሌ በበኩላቸው፣ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት መደበኛ የአሰራር ሥርዓቱን ለሚጠቀሙ ተቋማት ተደራሽ መደረጉን ገልጸው፣ የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት አጠቃቀምንም ሆነ ሌሎች አሰራሮችን በሚመለከት ባለሥስልጣን መስሪያ ቤቱ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን ሰርቷል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚያዚያ 16፡ 2017 ዓ.ም. የ2017 በጀት ዓመት የ9 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ ያቀረበው ደግሞ የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ነበር። የሚኒስቴሩን ሪፖርት ያቀረቡት ሚኒስትሯ ጫልቱ ሳኒ፣ በኮሪደር ልማት የመንገድ እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎችን በቅንጅት የማከናወን አቅም መፈጠሩን አንስተው፣ መንገዶችን በተመለከተም የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር ጠንካራ አደረጃጀት በመያዝ እየሰራ ነው ብለዋል:: ባለፉት ዘጠኝ ወራትም 14 ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት መለኪያዎችን መተግበር እንደጀመሩ የጠቀሱት ጫልቱ፣፣ የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔትም መስፋፋቱን ጠቅሰዋል ተብሏል። መንገዶች በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቃቸውን አስመልክቶ ከእንደራሴዎቹ በኩል ለተነሱት ጥያቄዎች የጋራ ምላሽ የሰጡት፣ የመንገድ አሥተዳደር ዋና ዳይሬክተሩ ኢኒጂነር መሐመድ አብዱራህማን እና ጫልቱ ሳኒ፣ የግንባታ ግብዓት ዋጋ መጨመር እና የካሳ ክፍያ መጓተት ለችግሮቹ ምክንያት መሆናቸውን በምላሻቸው ጠቅሰዋኣል። ችግሮቹን ለመፍታትም ነባር ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ላይ ትኩረት እንደተደረገም ጨምረው ገለጠዋኣል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶ።ር. እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ የከተማ ኮሪደር ልማት መስፋፋት እና የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቶች መቋቋምን እንደ ጥንካሬ ጠቅሰው፣ የመሬት ካዳስተር ሥርዓት ዝቅተኛ አፈጻጸም እና የክፍያ መዘግየትን ግን እንደ ድክመት አንስተው አብራርተዋል ተብሏል።

ሚያዚያ 20 ላይ ተረኛው የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈፃጸም አቅራቢ የነበረው ደግሞ የሰላም ሚኒስቴር ነበር። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የተጠቀሱትን ወራት ሪፖርት፣ ለምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡት የሰላም ሚኒስትሩ መሐመድ ኢድሪስ ሲሆኑ፤‘ርሳቸውም፣ የሚመሩት ተቋም በበጀት አመቱ 25 ሚሊዮን የኅኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማወያየት አቅዶ ከ18 ሚሊዮን የሚልቁትን ማወያየት መቻሉን ተናግረዋል። ሰላምን በዘላቂነት ለማምጣት ኅብረተሰቡን ማወያየት ቀዳሚው ተግባር መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ በየአካባቢው የሚከሰቱ ጥቃቅን ግጭቶችን ላይ ላዩን የብሄር እና የሃይማኖት መልክ ያለው በማስመሰል በተዛባ ግንዛቤ ግጭቱን ከማስፋፋት ይልቅ፣ የግጭቱን እውነተኛ መንስኤ መፈለግ እና መፍትሔ መስጠት የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነገዎ በበኩላቸው፣ ሚኒስቴሩ የአሰራር ሥርዓቶቹን በቴክኖሎጂ ለማዘመን የሰራቸው ሥራዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን ገልጸው፣ የቅድመ ግጭት ትንበያ ስራዎች በጥናት ላይ የተመሰረቱ ሆነው እንዲቀጥሉ ማሳሰባቸውን መረጃው ይጠቅሳል።



*ሚያዚያ 20 ላይ ተረኛው የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈፃጸም አቅራቢ የነበረው ደግሞ የሰላም ሚኒስቴር ነበር። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የተጠቀሱትን ወራት ሪፖርት፣ ለምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡት የሰላም ሚኒስትሩ መሐመድ ኢድሪስ ሲሆኑ፤ ርሳቸውም፣ የሚመሩት ተቋም በበጀት አመቱ 25 ሚሊዮን የኅኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማወያየት አቅዶ ከ18 ሚሊዮን የሚልቁትን ማወያየት መቻሉን ተናግረዋል።*

ሚያዚያ መገባደጃ ላይ የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን ለማቅረብ ተራው የደረሰው የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን፣ በእነዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 653.2 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ መቻሉን በዕለተ ቀኑ የተናገሩት ደግሞ የገቢዎች ሚኒስትሯ ዓይናለም ንጉሴ ነበሩ። ከእንደራሴዎቹ በኩልለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ የሰጡት ዓይናለም፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ጠንካራ የሆነ የአመራር እና የሠራተኛ ውስጣዊ ቅንጅት እንዲሁም ጠንካራ የሆነ የክትትል እና የድጋፍ ሥራዎች መኖራቸውን አብራርተዋል። በምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ደሳለኝ ወዳጄ በበኩላቸው፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ባከናወናቸው ቅንጅታዊ ሥራዎች ባለፉት 9 ወራት መንግስት ሊያጣው የነበረውን 88.85 ቢሊዮን ብር ወደ ገቢ በመቀየር አበረታች ሥራዎችን ስለማከናወኑ ገልጸዋል ተብሏል።

ከእነዚህ ተቋማት በተጨማሪም፣ የእንንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዕለተ-ሚያዚያ 29 የአራት ተቋማትን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለማድመጥ ወስኖ ነበር። በዕለቱ ቀዳሚ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ነበር። የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ ለምክር ቤቱ የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡትዋና ዳይሬክተር ጌታቸው መንግስቴ፣ በአሁኑ ወቅት 600 ሠራተኞች አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም፣ የሰው ኃይሉ በቂ ባለመሆኑ 100 የአየር ተቆጣጣሪዎች እየሠለጠኑ ነው ብለዋል። ኤርፖርቶችን በፍትሐዊነት ተደራሽ ለማድረግ ከታቀዱ ሰባት ኤርፖርቶች ውስጥ የኹለቱ ግንባታ መጠናቀቁን እና ቀሪዎቹ አምስቱ ደግሞ በግንባታ ላይ መሆናቸውን የጠቀሱት ደግሞየባለሥልጣኑ ኤር ናቪጌሽን ኮንስትራክሽን እና ኤርፖርት ታወር ግንባታ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ሀብታሙ አሸኔ መሆናቸውን መረጃው ይጠቅሳል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዶ በበኩላቸው፣ በአቬሽን ዘርፍ ከሁሉም አገራት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን ከጠንካራ አየር መንገድ ጀርባ ያለውን የአቬሽን ሥራ ማጠናከር እንደሚገባ በማንሳት በተሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት በትኩረት ሊሰራባቸው የሚገቡ አፈፃፀሞች በወቅቱ መከናወን እንደሚጠበቅባቸው አፅንኦት ተሰጥተዋል ተብሏል።

ሌላው በዚሁ ቀን የሥራ አፈፃፀም እና የአካባቢ አያያዝ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርቱን፣ ለምክር ቤቱ የመንግሥት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበው፣ በኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፖወር ኢኩዩፕመንት ማምረቻ ፋብሪካዎች ነበር።፤ የኤሌክትሪክ ኬብል፣ ትራንስፎርመር እና ሶላር ኃይል ማመንጫ ማዕከላትን በመገንባት ላይ የሚገኘው ተቋሙ፣ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ከምርት ሽያጭ እና ሌሎች ገቢዎች ለመሰብሰብ ካቀደው 5.5 ቢሊዮን ብር ውስጥ ማሳካት የቻለው የዕቅዱን 28 በመቶ ብቻ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ኮ/ል ሽጋው ሙሉጌታ ገልጸዋል። ተቋሙ በተቋማዊ የማሻሻያ ሂደት ውስጥ በመቆየቱ የምርት እና የገቢ ዕቅዱ እና አፈፃፀሙ እንዳይጣጣም አድርጎታልም ተብሏል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በአካባቢ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በሥራ ቦታ ደኅንነት እንዲኹም በንብረት አያያዝ እና አወጋገድ ላይ ክፍተቶች መስተዋላቸው መገለጹም ተዘግቧል።።

ሦስተኛው የዚሁ ቀን ሪፖርት አቅራቢ የነበረው ጤና ሚኒስቴር ሲሆን፣ የ2017 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቦ አስገምግሟል። የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ



የተከበሩ ወርቀሰሙ ማሞ፣ ጤና ሚኒስቴር ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የወባ እና ሌሎች ተዛማጅ ወረርሽኞችን ለመከላከል እና ለማከም የሄደበት ‘ርቀት በጥንካሬ የሚወሰድ ነው ብለዋል ተብሏል።ሰብሳቢዋ፣ የህክምና መሳሪያዎችን አገልግሎት ለማሻሻል እና በአንዳንድ ክልሎች ተበላሽተው የተቀመጡ መሳሪያዎችን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ሥልጠናዎችን በመስጠት ለጥገና ይመጣ የነበረውን ወደ 48. 7 ሚሊዮን የሚገመት ብር ማትረፍ መቻሉ ሌላው በጥንካሬ የሚነሳ ነው ሲሉም ተደምጠዋል።ሆኖም፣ የቤተሰብ እቅድ ተጠቃሚዎች ብዛት (ከታቀደው 81.7% ወደ 72% መውረዱ)፣ የፅኑ ህሙማን ክፍል የሞት ምጣኔ አለመቀነሱ፣ እንዲሁም በአፍላ ወጣቶች የሚከሰቱ እርግዝናዎች አለመቀነሳቸው (ከ13% ወደ 9% ለማውረድ ቢታቀድም) እንደ ድክመት ተለይተው ትኩረት እንዲሰጣቸው መጠቆሙን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

የቀኑ የመጨረሻ ሪፖርት አቅራቢ የነበረው፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሲሆን፣ በምክር ቤት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ የኮርፖሬሽኑን የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ገምግሟል። ቋሚ ኮሚቴውም፣ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሻገር ከተቀመጡ ግቦች መካከል አንዱ የሆነው የኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጤታማ መሆን እንዲችል ለሥራ እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ተለይተው ሊፈቱ እንደሚገባ አሳስቧል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ሥለሺ ኮሬ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ አዎንታዊ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ገልጸዋል። ኮርፖሬሽኑ፣ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ሼዶችን ለባለሀብቶች ከማስተላለፍ፣ የለማ መሬትን ወደ ሥራ ከማስገባት፣ መሠረተ ልማት ከማሟላት እና ከሥራ እድል ፈጠራ አኳያ ካከናወናቸው ጉልህ ተግባራት መካከል የጥንካሬ አፈጻጸሞች መሆናቸውንም ምክትል ሰብሳቢው አስገንዝበዋል ተብሏል። በኢንዱስትሪ ፓርኮች የስራ እድል ፈጠራ፣ በተኪ ምርት እና በመሰረተ ልማት ዝርጋታ የተሻለ ክንውን ቢታይም፤ በቆሻሻ ፍሳሽ አወጋገድ፣ በጥሬ እቃ አቅርቦት፣ በመሬት ይዞታ እና በገጽታ ግንባታ ዙሪያ ተኩረቶ ተሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባም ሥለሺ ማሳሰባቸው ተጠቁሟል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚው ዶ.ር. ፍስሐ ይታገሱ በበኩላቸው፣ በዐሥራ ሣስት ኢኮኖሚ ዞኖች እና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ72 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሆንም፣ በደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ማነስ እንዲሁም በቤት አቅርቦት እጦት ምክንያት ከፍተኛ የሠራተኛ ፍልሰት እንደሚስተዋል ተናግረዋል ተብሏል። የፋብሪካ ሠራተኞች ፍልሰት፣ የመሬት ይዞታ ይገባኛልነት እና የጥሬ እቃ አቅርቦት ቁልፍ ችግሮች ሲሆኑ፤ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሰራ እንደሆነም የኮርፖሬሽኑ አመራሮች አብራርተዋል።

በወሩ የመጨረሻ የ9 ወራት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን ለምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡት የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ነበሩ። የባህል እና ስፖርት ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ፣ ሚኒስቴሩ አንባቢ እና አሰላሳይ ትውልድ ለመፍጠር ሰፊ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ገልጸው፣ ከዚህ በተጨማሪም፣ “ኪነ-ጥበብ እና ሥነ-ጥበብ ለሕዝቦች አብሮነት እና ለገጽታ ግንባታ” በሚል መሪ ቃል፣ በክልሎች እና በከተማ አሥተዳደሮች ኪነ-ጥበብን ለብሔራዊ አንድነት እና ለአገር ትርክት ግንባታ በሚያስችል መልኩ ሰፋፊ ተግባራት መከናወናቸውን አስረድተዋል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወርቅሰሙ ማሞ በበኩላቸው፣ የተዘጋጁ እና ተደራሽ የሆኑ የብዝሃ-ባህል አካታችነት እና ማኅበራዊ ትስስር ልማትን የሚያግዙ ዶክመንተሪ ፊልሞች በመሥራት እና በማኅበራዊ ትስስር ዙሪያ አውደ ጥናት በማካሔድ፣ የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቋንቋዎችን በማልማት፣ ተጠቃሚነትን እና ተደራሽነቱን በማሳደግ ረገድ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች በጥንካሬ የሚታዩና ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው አመላክተዋልም ተብሏል።

# የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ ወርኃ ሚያዝያን ያሳለፉት፣ ሚዲያውን የተመለከተውን ሕግ በማውጣት እና ረቂቅ ሕግጋቱንም በመመርመር አልያም የተቋማቱን የሥራ ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም አልነበረም። እንድራሴዎቹ፣ 45 የሚሆኑ የመስክ ጉብኝቶችን ጨምሮ፣ የተለያዩ የፌዴራል እና ክልላዊ ተቋማትን አኹናዊ ኹኔታም በተወካዮቻቸው በኩል ጎብኝተዋል።

## የተቋማት ጉብኛቶች

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ የመሩት ከፍተኛ የልኡካን ቡድን፣ ሚያዝያ 20 2017 ዓ.ም. መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ጎብኝቷል። የጉብኝቱ ዋነኛ ዓላማም፣ ማዕከሉ በዜጎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ በቅርበት ለመመልከት እና የሥራ ሂደቱን ለመገምገም ነበር ተብሏል። ማዕከሉ የዜጎችን ጊዜ እና ጉልበት ለመቆጠብ በማሰብ፣ ከ12 የተለያዩ የመንግስትተቋማት የተውጣጡ 41 አገልግሎቶችን በአንድ ጣሪያ ሥር እንደሚያቀርብ መግለጹን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። ይህም ለኅብረተሰቡ ፈጣን እና ቅልጥፍና ያለው አገልግሎት ለመስጠት ያለመ ነው የተባለ ሲሆን፣ በዘመናዊ የሥራ አፈጻጸም ዘዴዎች አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝም ተጠቅሷል።

የምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በበኩሉ፣ በጠቅሰነው ሚያዝያ ወር በፋይናንስ እና ገቢዎች ዘርፍ ላይ ሦስት ጉብኝቶችን አድርጓል። በወሩ መጀመሪያ ላይ የገንዘብ ሚኒስቴርን የጎበኘው ኮሚቴው፣ የሚኒስቴሩን የ8 ወራት አፈጻጸም በዝርዝር ገምግሟል ተብሏል። በዚህ ወቅት የግብር ፖሊሲ እና አፈጻጸም ክትትል ክፍሎችን፣ የታደሱ ቢሮዎችን፣ ዳታ ሴንተርን፣ ካፌቴሪያዎችን እና ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ ያሉ ታሪካዊ ሰነዶችን የያዘ ቤተ መጻሕፍትን የመጎብኘት ዕድልም ማግኘቱን መረጃው ጠቅሷል። ከገንዘብ ሚኒስቴር በተጨማሪ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤትን የጎበኘው ይኸው ኮሚቴ፣ በጉብኝቱ ወቅትም የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱን የ9 ወራት ሪፖርት አድምጧል። ሪፖርቱም፣ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ 1.8 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ መቻሉን እና ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ46.44% ዕድገት እንዳለው አሳይቷል ተብሏል በሚያዝያ 8 ቀን፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ጅማ ቅርንጫፍን የጎበኘው በሦስተኛነት የጎበኘው ኮሚቴው፣ በቅርንጫፉ ኃላፊዎች አማካኝነት ኮንትሮባንድን ለመከላከል እና የግብር አሥተዳደርን ለማዘመን እየተጠቀሙባቸው ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ ቀርቦለታል ተብሏል።

የምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ቋሚ ኮሚቴ በበኩሉ፣ ሚያዝያ 1 ቀን 2017 ዓ.ም. የውኃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን መጎብኘቱ ተዘግቧል። ኮሚቴው በ2016 ዓ.ም. በተሰጠው ምክር መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸም ገምግሟል። በግምገማው ወቅት የሠራተኞች ምልመላ 30% ብቻ መሆኑን እና የበጀት እጥረት ችግር መኖሩን በመጥቀስ፣ ለተቋሙ ኃላፊዎች ችግሩን ለመፍታት ተገቢው ትኩረት እንዲሰጥበት ጥያቄ ማቅረቡን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ወጪ፣ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት፣ በፋይናንስ ቁጥጥር እና በአደጋ ሥጋት አመራር ላይ ትኩረት አድርጎ የተካሄደው ጉብኝት ደግሞ ሌላይኛው የወሩ የእንደራሴዎቹ ክንውን ነበር። ድሬ ዳዋ የሚገኘውን የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝን የጎበኘውኮሚቴው፣ የኢንተርፕራይዙን የሥራ እንቅስቃሴ በ2014 ዓ.ም. የፌደራል ኦዲተር የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሠረት ገምግሟል ተብሏል። የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የድሬዳዋ ቅርንጫፍን የ2014 ዓ.ም. የሒሳብ ሕጋዊነት ኦዲት ግኝቶችን መነሻ በማድረግ መገምገሙ የተሰማው ኮሚቴው፣ ኢንተርፕራይዙ የዋና ኦዲተርን ግኝቶች መሠረት በማድረግ የወሰዳቸውን የማሻሻያ እርምጃዎች እና ቀጣይ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የተዘረጋውን ሥርዓትም እንዲሁ ተመልክቷል ተብሏል።

የፍል ውኃ አገልግሎት ድርጅት ላይ የተደረገው ጉብኝትም ሌላው የወሩ ክንውን ነበር። ድርጅቱን የጎበኘው፣ በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ድርጅቱ በቀን ከአምስት ሺህ በላይ ደንበኞችን እያስተናገደ በተወሰነው ታሪፍ መሰረት ገቢ እየሰበሰበ መሆኑን አረጋግጧል ተብሏል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅትን የጎበኘው ይኸው ኪሚቴ፣ የመልዕክት አገልግሎቶችን፣ የደንበኞች አገልግሎትን እና የካሜራ መቆጣጠሪያ ክፍሎችን ቦታው ተገኝቶ ተመልክቷል ተብሏል። የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዳግማዊ ኃይልዬ፣ ለደንበኞች ፈጣን እና ዘመናዊ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣



የክልል አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ለማግኘት ቋሚ ኮሚቴው አገዛ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋልም ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን መጎብኘቱ ደግሞ የወሩ የመጨረሻው የእንድራሴዎቹ የተቋማት ጉብኝት ነበር። የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሠይፈ ደርቤ፣ አገልግሎቱ በአገር ውስጥ እና በውጭ ቋንቋዎች የሠለጠኑ ባለሙያዎችን በማሰማራት እየሠራ መሆኑን ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት አስረድተዋል። ኮሚቴውም በምልከታው፣ ኤጀንሲው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብሩ ሥራዎችን በማከናወን ረገድ ያለውን ሚና ማረጋገጡን ከዚኹ ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።

## የመስክ ጉብኝቶች

በወርኃ ሚያዚያ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ሰፋ ያሉ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የመስክ ጉብኝቶችን አድርገዋል። የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚያዝያ ወር በፍትሕ እና ማረሚያ ተቋማት ላይ ትኩረት ያደረጉ ጉብኝቶችን አከናውኗል። ኮሚቴው፣ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙትን የሸገር ከተማ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን በመጎብኘት፣ ፍርድ ቤቶቹ እውነትን በማቅረብ እና ፍትሕን በማስፈን የኅብረተሰቡን እምነት ለመመለስ የሚያደርጉትን ጥረት በመስክ ጉብኝቱ ተመልክቷል። ከሸገሩ በተጨማሪም፣ ኮሚቴው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትንም ጎብኝቷል፤ የፍርድ ቤቱ ኃላፊዎች፣ ለቋሚ ኮሚቴው አባላት በቴክኖሎጂ ትግበራ ዙሪያ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን አብራርተዋል ተብሏል። ኮሚቴው በበኩሉ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ለሚገኙት ወጣት የሕግ ታራሚዎች የዕርምት ጊዜያቸውን እስኪጨርሱ በተለያዩ የሙያ ተግባራት እንዲሰማሩ ዕድል ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ አሳስቧል ተብሏል።

የምክር ቤቱ የንግድ እና ቱሪዝም ቋሚ ኮሚቴ፣ ከንግድ እና ቱሪዝም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያደረጋቸው በርካታ ጉብኝቶችም የሚጠቀሱ ናቸው ። ኮሚቴው፣ ባሕር ዳር የሚገኘውን ኤም.ኤስ.ኤ ቢዝነስ ግሩፕን በመጎብኘት፣ ድርጅቱ የውጭ ምርቶችን በአገር ውስጥ በሚታሸጉ እና በሚታከሉ ምርቶች ለመተካት 468 የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየተገበረ መሆኑን ተመልክቷል። በባሕር ዳር ክልል ለሆርቲካልቸር ምርቶች የተተከለው ትራንስፎርመር ያጋጠመው የብልሽት ችግር ከአማራ ክልል መንግሥት ጋር እየተመረመረ መሆኑን ኮሚቴው ተረድቷል ተብሏል። የኢትዮጵያ ምርት ገበያንም የጎበኘው ኮሚቴው፣ የኤክስፖርት ምርት አማራጮችን ለማበልፀግ በአገር ደረጃ 26 አዳዲስ ቅርንጫፎች መከፈታቸውን እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎቶች መሰጠታቸውን መረዳት ችሏል። በመጨረሻም፣ ይኸው ኮሚቴ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርን እና ተያያዥ ተቋማቱን (ማለትም፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት፣ ነዳጅ እና ኢነርጂ እና ተስማሚነት ምዘና) በመጎብኘት የሥራ ሁኔታቸውን እና ተግባራቸውን ተመልክቷል ተብሏል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ በዚሁ ሚያዝያ ወር፣ በግብርና ልማት ላይ ዙሪያ ሰፊ የመስክ ምልከታዎችን አድርጓል ተብሏል። በቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚከናወኑ የአረንጓዴ አሻራ እና የልማት ትሩፋት ሥራዎችን በገመገመበት ወቅትም፣ ስለ አረንጓዴ አሻራ እና ተያያዥ ልማቱ ዙሪያ የ9 ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ቀርቦለታል። በአሶሳ ዞን በመንግስት እና በኅኅብረተሰብ መሪነት እየተከናወኑ ያሉ የግብርና ሥራዎችን በመስክ ጉብኝቱ የተመለከተ ሲሆን፣ የውኃ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውልም ማሳሰቡ ተዘግቧል። በአፋር ክልል የእንስሳት ማድለብ ሥራዎችን እና የተጠቃሚዎች ንቁ ተሳትፎ መኖሩንም ኮሚቴው መግለጹ ተጠቅሷል። በወሩ ማጠናቀቂያ፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ የቡና ላኪ ድርጅቶችን (ዳዬ ቤንሳ እና ቴስቲ ስፔሻሊቲ ኮፊ የተሰኙትን) የጎበኘው ኮሚቴው፣ ዘግየት ብሎም የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለሥስልጣንን ሲጎበኝ፣ በዚያ ጉብኙቱምየባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤቱን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸምን ገምግሞ፣ ከጉብኝቱ ቀጣይ ባለው ሳምንት የሚጀመረውን ነጻ ስልክ ጥሪ አገልግሎትንም ጨምሮ መመልከቱን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ዘገባዎች አመልክተዋል።

የከተማ መሠረት ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም፣ የመሠረተ ልማት እና የትራንስፖርት ፕሮጀክቶችን ጎብኝቷል። ኮሚቴው በአፋር ክልል እየተከናወኑ ያሉ የመሠረተ ልማቶች፣ የሴፍቲኔት ሥራዎች እና የሰመራ ከተማ የኮሪደር ልማት እንቅስቃሴን በቅርበት ሊመለከት ችሏል። በተለይም ኮሚቴው የጎበኘው 70 ኪ.ሎ. ሜ. ‘ርዝማኔ ያለውን የሚሊዶኒ መገንጠያ የማንዳ ቡሬ (አሰብ ኮሪደር) የመንገድ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ፕሮጀክቱም ለድንበር አካባቢዎች



እና ለአገሪቱ የወጪ እና ገቢ ንግድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስምሮበታል ተብሏል። የኢትዮጵያ መንገዶች አሥተዳደር ማሠልጠኛ ማዕከልን በመጎብኘት የማዕከሉን የምርምርና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ተመልክቶ ከአመራሮች ጋር መወያየቱ የተሰማው ኪሚቴው፣ የነዳጅ እና የሲሚንቶ አቅርቦት ጉዳይ የፌደራል መንግሥቱ ትኩረት መሆኑን ማስገነዘቡ ተጠቅሷል።

የምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ቋሚ ኮሚቴ. በጤና፣ በማኅበራዊ ልማት እና በባህል ዘርፍ ላይ ያደረጋቸው በርካታ ጉብኝቶም እንዲሁ የወርኃ ሚያዚያ ተጠቃሽ ክንውን ነው። ኮሚቴው፣ የሁለገብ ዓይነ ስውራን እና አካል ጉዳተኞች ማሠልጠኛ እና ማቋቋሚያ ማኅበርን በመጎብኘት፣ በአሁኑ ወቅት 68 አካል ጉዳተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን እና ሦስት የገቢ ማስገኛ ኅንፃዎችም ግንባታ ላይ መሆናቸውን ተመልክቷል ተብሏል። አለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልን በመጎብኘትም የቀዶ ሕክምና፣ የመድኃኒት አቅርቦት እና የእናቶችና ጨቅላ ሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን መገምገሙ ተጠቅሷል። በአዲስ አበባ የሚገኘው የ20ኛው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከልም ለተለያዩ ማኅበረሰቦች የምገባ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ኮሚቴው አረጋግጫለሁ ብሏል። በሱማሌ ክልል ጉብኝቱ ደግሞ፣ የገረብ አሌ ወረዳ አየር ደጋ ጤና ጣቢያን እና የካራማራ ሆስፒታልን አገልግሎት አሰጣጥ ገምግሟል፤ በተለይ በካራማራ ሆስፒታል ዲጂታላይዝድ የታካሚ መረጃ ሥርዓት መተግበሩን አድንቋል ተብሏል። የሱማሌ ክልልን የኪነ-ጥበብ ቡድን እና ሙዚየምን በመጎብኘት ቅርሶችን የመሰብሰብ እና የማደራጀት ተግባር በአዎንታዊ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ተምልክቼያለሁ ያለው ኮሚቴው፣ የባህል እና ቱሪዝም ምክትል ቢሮም ባህላዊ እሴቶችን ለትውልድ ለማስተላለፍ እየሰራ መሆኑን ገልጿል ተብሏል። በተጨማሪም፣ አካል ድጋፍና በማሽን የሚደረግ ህክምና የሚሰጥበትን የአካል ተሀድሶ ማዕከልን፣ የቱሊ ጉሌድ ወረዳ ቱሊ ጤና ጣቢያን፣ እንዲሁም በጀረር ዞን አራርሶ ወረዳ የሚገኙትን የዲክሪሌ ጤና ኬላን፣ አራርሶ ጤና ጣቢያን፣ የሴቶች እና ሕፃናት ልማት ማዕከልን እና የስፖርት ማዘዣ ስፍራዎችን በሚያዚያ ወሩ የመስክ ጉብኝቱ ከተመለከታቸው ውስጥ እንደሚገኙበት መረጃው ያመለክታል።

በሕዝብ ተወካዬች ምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በበኩሉ፣ በወርኃ ሚያዝያ ዓ.ም. የትምህርት እና የሰው ሀብት ልማትን ዘርፎችን ገምግሟል። ኮሚቴው ቀብሪ ደኻር ዩኒቨርሲቲን በመጎብኘት ለመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ቢገለጽም፣ የተሽከርካሪ፣ የላብራቶሪ ግብዓት እና የበጀት እጥረት ዋንኛ ችግሮች መሆናቸውን በዚያ ጉብኝቱ አንስቷል ተብሏል። የሶማሌ ክልል ትምህርት ቢሮንም የጎበኘው ኮሚቴው፣ ቢሮው የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል እየሰራ ቢሆንም፣ የመምህራን እጥረት ችግር አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን በመስክ ጉብኝቱ ተመልክቷል ተብሏል።

ሌልይኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የማዕድን እና ኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በዚሁ ሚያዚያ ወር፣. በማዕድን እና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረጉ ጉብኝቶችን ማድረጉን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።። በአፋር ክልል አፍዴራ ዞንን የጎበኘው ኮሚቴው፣ የቲቲአር ጨው ፋብሪካ ቢዘጋም፣ የኢሲዲ ጨው ፋብሪካ ግን በሙሉ አቅሙ እያመረተ መሆኑን ተመልክቷል ተብሏል። ከዚህ በተጨማሪም፣ 160,000 ቶን አቅም ያለው የቤንቶናይት ማዕድን ማውጫ፣ በዐቅሙ ልክ እንዳያመርት (ወደ አገር ውስጥ ያልገቡ ማሽኖች በመኖራቸው የሥራ እንቅፋት እንደገጠመው ታውቋል ተብሏል። ኮሚቴውም የውጭ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች መተካት አስፈላጊ መሆኑን ማሳሰቡ ተዘግቧል። በመጨረሻም፣ በአፋር ክልል ከሚገኙ 25 አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል 19ኙ ከማሻሻያው በኋላ በኋላ ሥራ ቢጀምሩም፣ ከ9 ያላነሱት ፋብሪካዎች በመሬት መንቀጥቀጥ እና በሌሎች ምክንያቶች እንደተዘጉ ኮሚቴው አረጋግጫለሁ ብሏል።

የወሩ መገባደጃ የመስክ ጉብኝት የተደረገው፣ በምክር ቤቱ የማኅበራዊ ዋስትና ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ሲሆን፣ ኮሚቴው በጅማ ዞን የሚገኙ የመንግስት ሠራተኞችን ጎብኝቷል ተብሏል። በጉብኝቱ ወቅት፣ በዞኑ ያሉ የመንግስት ሠራተኞች በማኅበራዊ ዋስትና መመዝገባቸውን አረጋግጫለሁ ያለው ኮሚቴው፣ በአፋር ክልልም እንዲሁበማኅበራዊ ዋስትና ዙሪያ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን መግለጹን የምክር ቤቱ ዘገባ አመልክቷል።



# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በሚያዝዚያ ወር ያከናወነው ፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ሥራ አንድ ብቻ ነበር።፤ ይኸም፣ በግሪክ የፓርላማ አባል እና የኦርቶዶክስ ኢንተርፓርላመንት ጉባኤ ኃላፊ ዶ.ር. ማክስሞስ ቻራኮፖሎስ የተመራውን የልኡካን ቡድን የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና በምክር ቤቱ የኢትዮጵያ እና የምዕራብ አውሮፓ አገራት እንዲሁም የአውሮፓ ኅብረት የወዳጅነት ኮሚቴ አባላት ያደረጉት ውይይት ነበር።። በውይይቱ ላይ አፈ-ጉባኤ ታገሰ ፣ ኢትዮጵያ ከግሪክ ንግድ እና መዋዕለ-ንዋይን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች ልምድ ለመቅሰም ፍላጎት እንዳላት ጠቅሰው፣ ያላትን ተሞክሮም ለማካፈል ዝግጁ ናት ብለዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ እና የምዕራብ አውሮፓ አገራት የወዳጅነት ኮሚቴ ሰብሳቢው አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው፣ የኹለቱ አገራት የረጅም ጊዜ ወዳጅነት ይበልጥ ማደግ እንዳለበት አጽንዖት ሰጥተው፣ አገራቱ በቴክኖሎጂ፣ ንግድ፣ ግብርና፣ ቱሪዝም እና ኢነርጂ ዘርፎች ቢተባበሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጠቁመዋል ተብሏል። የግሪክ ልኡክ አባል የሆኑት ማክስሞስ በበኩላቸው፣ አገራቸው በኮንስትራክሽን፣ በባሕር ትራንስፖርት እና በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዘርፎች ያላትን ልምድ ለኢትዮጵያ ለማካፈል ፈቃደኛ መሆኗን ገልጸው፣ የግሪክ ባለሀብቶችም በኢትዮጵያ ያላቸውን የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትእንዲያሳድጉ ጥሪ ማቅረባቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

# የቋሚ ኮሚቴ አመራሮች ስየማ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የተወካዮች ምክር ቤት፣ በሚያዚያ 21 ቀን 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በ27ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በምክር ቤቱ የተጓደሉ የቋሚ ኮሚቴ አመራሮችን ሰይሟል። በዚህም፣ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዱ የከተማ፣ መሰረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዲሁም የተከበሩ መለስ መና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነው ተሰይመዋል።፤ በተከበሩ ታገሰ ጫፎ የቀረበውን የስየማ የውሳኔ ሐሳብም፣ ምክር ቤቱ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል።

# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች

01 የግብርና ጉዳዮች

02 የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች

03 የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች

04 የሰው ሃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች

05 የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች

06 የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች

07 የከተማ መሠረት ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች




08 የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት እና ባህልና ስፖርት ጉዳዮች

09 የመንግስት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች

10 የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች

11 የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች

12 የዲሞክራሲ ጉዳዮች

13 የመንግስት የልማት ድርቶች ጉዳዮች

# የሴት እንደራሴዎቹ ግምገማ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴት ተመራጮች ኮከስ፣ ባለፉት ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ያከናወናቸውን ተግባራት እና ውጤቶች የገመገመበት ሁነት ደግሞ ሌላይኛው የሚያዚያ ወር የምክር ቤቱ ክራሞት ነበር። የኮከሱ ሰብሳቢ የተከበሩ ኪሚያ ጁንዲ ለኮከሱ ባቀረቡት ሪፖርት መሠረት፣ ኮከሱ ከምክር ቤታዊ ተልዕኮው ባሻገር፣ ለሴት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የክህሎት ሥልጠና ሰጥቷል ብለዋል። የሴቶች ኮከስ የበላይ ጠባቂዋ የተከበሩ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ ኮከሱ በአገር ውስጥ በተከሰቱ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ለተጎዱ ዜጎች 65 ሚሊዮን ብር ግምት ያለው የቁሳቁስ ድጋፍ በማሰባሰብ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በብቃት ተወጥቷል ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪም በሴቶች አቅም ግንባታ፣ በሥርዓተ ፆታ አካቶ ትግበራ፣ በኮከሱ መረጃ አደረጃጀት እና የገጽታ ግንባታ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ውጪ የልምድ ልውውጦች ላይ የተሰሩት ሥራዎች እና የተገኙት ውጤቶች በዝርዝር ቀርበው ውይይት እንደተደረገባቸው ለመረዳት ተችሏል።

# የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ

## በመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ ቁጥር 1374/2017 ዙሪያ

ሚያዝያ 9 ቀን 2017 ዓ.ም. 25ኛ መደበኛ ስብሰባውን ያደረገው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የበዛ ትችትን ያስተናገደ አንድ ዐዋጅን አጽድቋል። ምክር ቤቱ፣ የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ ቁጥር 1374/2017 የተሰኘውን ይኽን ማሻሻያ ዐዋጅ፣ ቀድሞ የነበረውን የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ ቁጥር 1238/2013ን በዐሥራ አንድ ጉዳዮች አሻሽሎ በአንድ ተቃውሞ በአብላጫ ድምፅ አፅድቆታል።

## ከትናንት በስቲያ

በሃያኛው ክፍለ-ዘመን መባቻ የጀመረው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን፣ መቶ ዓመታት ባለፈው ታሪኩ የተለያዩ ምዕራፎችን አልፏል። እስከ 1966ቱ አብዮት ድረስ አጼ ኀይለ ሥላሴ የጀመሯቸውን አገሪቷን የማዘመን ሙከራዎች ቅርጽ በመስጠት የጀመረው፣ በተለይም የጋዜጦቹ አበርክቶ ጥቂት ዘግየት ብሎ ንጉሡን በማወደስ ራሱን ገድቧል። በዋናነት ኢኮኖሚያዊ የሥርዓት ማሻሻያዎችን ሲገፋ የነበረው የሚዲያው መንገድ፣ የአጼው ሥርዓት መወርዛት ሲጀምር፣ እርሱም አብሮ መዳከም ጀመረ። በሂደትም፣ የ1996ቱ አብዮት ሲገነፍል፣ እንደሌሎቹ የአገሪቷ ኹሉም መልኮች ኹሉ፣ ሚዲያውም በሥር-ነቀል ሐሳቦች ተሞላ። ያም ሆኖ፣ አብዮቱን ተከትሎ ወደ ሥልጣን የመጣው ደርግ፣ በንጉሡ ዘመን በጭላንጭል የነበረውን የመናገር እና በተለይም የለውጥ አራማጅ ምሁራን ይባሉ በነበሩት የሃያኛው ክፍለ-ዘመን አሻሳይ ጸሓፍት ክርክር እንኳን የሚካሄድበትን ምኅዳር ሙሉ ለሙሉ ዘጋው። ከዚኽ መሰሉ ቅጥ ያጣ የመናገር ነፃነት አፈና 17 ዓመታት በኋላ ወደ ሥልጣን የመጣው ኢሕአዴግ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ እስከ አኹንም የሚወደስለትን አንድ አዲስ ዐዋጅ አስተዋወቀ።

አኹን አገሪቷ የምትመራበት ሕገ-መንግሥት ከመውጣቱ ኹለት ዓመታት በፊት፣ በያኔው የሽግግር መንግስት አማካኝነት የወጣው የፕሬስ ነፃነት ዐዋጅ ቁጥር 34/1985፣ ቅድመ-ምርመራን በሕግ በመከልከል የመፃፍን ነፃነት ሰጥቷል ሲሉ ብዙዎች በግዙፍ የታሪክ ምዕራፍነቱ ያወድሱታል። ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብት በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር መረጋገጡን የሚጠቅሰው ይኸው ዐዋጅ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ኹሉ ሕዝቡ የመንግሥትን ሥራ ለማወቅ ያለውን መብት እና የተጠያቂነት መርህ በመከተል ከፕሬስ ጋር የመተባበር ግዴታ እንዳለባቸው ደንግጎ ነበር። ይኽንን እና ሌሎች ዜጎች በሚመለከቷቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሚዛናዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በመንግስት አመራር ላይ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ፕሬሱ ያለውን ሚና 'ጉልህ' ሲል የሚጠራው የ85ቱ ዐዋጅ፣ ለዚኹ ኹሉ ግብር ቅድመ-ምርመራ አልያም ሴንሰርሺፕ መቅረቱን አውጇል። ይኽን አውጃ ተከትሎም፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የግል ጋዜጦች እና መጽሔቶች በዋናነት ዋና ከተማዋንሞሏት። ይኽ የግል ሚዲያ መስፋፋትም፣ ቀስ በቀስ ወደ ራዲዮ እና ቴሌቪዥንም ተሻግሮ፣ ኢትዮጵያ ከሃይማኖት እስከ ፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ እስከ ማኅበራዊ ጉዳዮች የሚሸፍኑ በርካታ መገናኛ ብዙኃንን አይታለች።

ጅማሮውን 1985 ላይ የሚያደርገውን የግል መገናኛ ብዙኃን ለመግራት በሚልም፣ ባለፉት ሦስት ዐሥርታት የተለያዩ ዐዋጆች ጸድቀዋል። የ85ቱን ዐዋጅ ተከትሎ፣ የብሮድካስት ዐዋጅ 178/1991፣ የብሮድካስት አገልግሎት ዐዋጅ ቁጥር 533/1999፣ የመገናኛ ብዙኃን የመረጃ ነጻነት ዐዋጅ ቁጥር 596/2000፣ የማስታወቂያ ዐዋጅ ቁጥር 759/2004፣ የጥላቻ ንግግር እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ዐዋጅ ቁጥር 1185/2012፣ እና የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ ቁጥር 1238/2013 ዐዋጆች፣ ሊጠቀሱ የሚችሉ የቀደሙ ዐዋጆች ናቸው።

## ለምን ተሻሻለ?

በዕለተ ሚያዚያ ዘጠኝ በምክር ቤቱ የተገኙት 248 እንደራሴዎች በአብላጫ ድምፅ ያጸደቁት ማሻሻያ ዐዋጁ፣ በዐዋጁ እና በተቋሙ አደረጃጀት ምክንያት ተዳክሟል የተባለውን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሚያጠናክር ነው የሚለው ለዐዋጁ መሻሻል የተሰጠው ቀዳሚው ምክንያት ነበር። የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጁ ፀድቆ በሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም፣ ዐዋጁ ተግባራዊ ሲደረግ ከመገናኛ ብዙኃን የቁጥጥር ሥልጣን እና ተግባራት



አንጻር ተስተውለዋል የተባሉ አሠተዳደራዊ ክፍተቶችን በማስተካከል ዘርፉን በአግባቡ ለማሥተዳደር እንዲቻል ዐዋጁ እንዲሻሻል መደረጉም ተገልጿል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ነባሩ ዐዋጅ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የዕለት ተዕለት ሥራውን እንዳያከናውን ለተቋሙ ቦርድ የተሰጠው ሥልጣን የሕግ ክፍተት ያለበት በመሆኑ እና ያንን ለተቋሙ ሥራ አሥፈፃሚ መመለስ አስፈላጊ በመሆኑ ማሻሻል እንዳስፈለገም አክሎ አብራርቷል። በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የዐዋጁ መሻሻል መገናኛ ብዙኃኑን በማጠናከር ገለልተኝነታቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል እንደሆነ ተናግረዋል ተብሏል። መንግስት የተቋማት ገለልተኝነት ላይ የሰራቸው ሥራዎች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣታቸውን የጠቀሱት ተስፋዬ፣ ባለፉት ዓመታት በዘርፉ መንግስት ያደረጋቸው ማሻሻያዎች በአገሪቱ ያለው ሚዲያ በዓይነት፣ በስፋት እና በተደራሽነት መጨመሩን ተናግረዋል። መንግስታቸው ከመራው ፖለቲካዊ ለውጥ በፊት 122 የነበረው የሚዲያ ቁጥር ወደ 272 ከፍ ብሏል ያሉት ተጠሪ ሚኒስትሩ፣ 25 ብቻ የነበረው ቴሌቪዥን ወደ 103፣ 52 የነበረው ሬዲዮ ወደ 125 ማደጉን እና ሚዲያዎች ከሚጠቀሟቸው ቋንቋዎች አንጻርም ከ29 ወደ 58 ከፍ ማለቱን ለእንደራሴዎቹ አስታውሰዋቸዋል። አክለውም፣ የዐዋጁ መሻሻል እነዚህ ሚዲያዎች በኃላፊነት እንዲንቀሳቀሱ እና ለአገር ግንባታ የሚኖራቸውን ድርሻ ይበልጥ ከፍ እንዲያደርጉ የሚያግዝ ነው ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ዮናታን ተስፋዬ በበኩላቸው፣ ማሻሻያው፣ የአደረጃጀት ጉዳዮችን የተመለከቱ የነባሩን ዐዋጅ ክፍሎች ማሻሻል ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ሲሉ ተደምጠዋል። ለዚኽም፣ በአገሪቷ ውስጥ ያሉትን ግጭቶች እና ቀጣዩን ብሔራዊ ምርጫ በምክንያትነት ያነሱት ዳይሬክተሩ፣ ግጭቶቹ ደግሞ እየተቀጣጠሉ ያሉት

*አኹን አገሪቷ የምትመራበት ሕገ-መንግሥት ከመውጣቱ ኹለት ዓመታት በፊት፣ በያኔው የሽግግር መንግስት አማካኝነት የወጣው የፕሬስ ነፃነት ዐዋጅ ቁጥር 34/1985፣ ቅድመ-ምርመራን በሕግ በመከልከል የመፃፍን ነፃነት ሰጥቷል ሲሉ ብዙዎች በግዙፍ የታሪክ ምዕራፍነቱ ያወድሱታል።*

በሚድያው በኩል ነው ሲሉ ወቀሳቸውን አሰምተዋል። ዮናታን፣ ወደፊት ከምርጫው ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለውን ኹኔታም ማሻሻያው ታሳቢ ማድረጉን መናገራቸውም ተዘግቧል።

## ምን ተሻሻለ?

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ከላይ በጠቃቀስናቸው መነሾች በአብላጫ ድምጽ እንዲሻሻል የወሰነበት ዐዋጅ፣ መሠረታዊ የሚባሉ ማሻሻያዎችን ያደረገ ነበር። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሥራ አመራር ቦርድ በወሳኝ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ የሚያስችሉ ማሻሻያዎች መደረጋቸውን የሚያነሳው ለእንደራሴዎቹ የቀረበው የማሻሻያ ማብራሪያው፣ በመርህ ደረጃ የባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ቦርድ ባለሥልጣኑን በፖሊሲ የሚመራ አካል ቢሆንም፣ በዐዋጁ አንቀፅ 13(2) መሰረት በዕለት ተዕለት የሚከወኑ የቁጥጥር ሥራዎች በቦርድ እንዲከናወኑ መደረጉን ያነሳል። ከዚህ አኳያም፣ አንቀፅ 9/5/ሀ/ የቦርዱ አባላት ለመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ቅርበት እና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ አካላት እና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ ሲልም፣ በማብራሪያው መሰረት የተሻሻለውን ድንጋጌ ይጠቅሳል። የቀድሞው የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ 5/ሀ የቦርዱ አባላት፣ ኹለቱ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ኹለቱ ከመገናኛ ብዙኃን እና ኹለቱ ለመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ጠቀሜታ እና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ ተቋማት እና የኅብረተሰብ ክፍሎች ይሆናሉ የሚል ሲሆን፤ አዲሱ የተሻሻለው ዐዋጅ በበኩሉ፣ የቦርዱ አባላት ለመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ቅርበት እና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ አካላት እና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ በሚል እንዲተካ ተደርጓል። ከዚያ ባለፈም፣ አንቀጽ 5/ለ ላይ፣ ሦስቱ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት የተውጣጡ ይሆናሉ የሚለው ድንጋጌ ግን እንደነበረ ይቀጥላል ተብሏል። ነገር ግን፣ የባለሥልጣኑ የቦርድ አባላት ስብጥር ከሁሉም አካላት መሆን አለበት በሚል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሆኑ ሰዎች የዚህ ተቋም የቦርድ አባል መሆን አይችሉም በሚል ተደንግጎ የነበረው አንቀጽ ተሽሮ፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሆኑ ሰዎች የተቋሙ ቦርድ አባል እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ማሻሻያ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አጽድቆታል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አሿሿምን በተመለከተ የተደረገው ማሻሻያ በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው የማሻሻያው ክፍል ነው። በነባሩ ዐዋጅ፣ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርዱ ተመልምሎ በመንግስት አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየም ነበር፤ በማሻሻያው መሰረት ግን፣ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሾም ተደንግጓል። በሚዲያዎች ፈቃድ ዙሪያም የተደረገው ማሻሻያ ተጠቃሽ ሆኗል። በነባሩ ዐዋጅ፣ ከፈቃድ አለማደስ እስከ ማገድ አልያም የፈቃድ መሠረዝ የሚያስከትሉ ውሳኔዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ነበር፤ በሚያዚያው ማሻሻያ ግን ይህ ኹሉ ሥልጣን ወደ ባለሥልጣኑ ዞሯል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱም፣ አንድን ፕሮግራም እስከማገድ የደረሰ ውሳኔ የመወሰን ሥልጣን በማሻሻያው ተሰጥቶታል። ነባሩ ዐዋጅ፣ ቦርዱን በዕለት ተዕለት የቁጥጥር

ሥራ ላይ ገድቦት በመቆየቱ፣ በሕግ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም ወቅቱን የጠበቀ ውሳኔ መስጠት እንዳይችል አደርጎታል የሚለው ለዚኽ ማሻሻያ ከቀረቡት ምክንያቶች መካከል አንዱ ነበር። ፈቃዱ ያልታደሰለት አልያም የተሰረዘበት የመገናኛ ብዙኃን፣ ለቀረበበት ክስ ምላሽ የሚሰጥበት ቀነ ገደብም ከተሻሻሉት ድንጋጌዎች መካከል ይገኝበታል፤ በነበረው ዐዋጅ፣ የተጠቀሰው የመገናኛ ብዙኃን ምላሹን በጹሑፍ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው እንደሚገባ ተደንግጎ ነበር፤ አዲሱ ዐዋጅ ግን፣ ባለሥልጣኑ በወሰናቸው ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ የመገናኛ ብዙኃን ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ እንደሚችል እና ቦርዱም አቤቱታው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት በሚል ማሻሻያ ተደርጎበታል።

የቀጥታ ስርጭትን የተመለከተው ርዕሰ ጉዳይም ሌላይኛው የተሻሻለው የዐዋጁ ክፍል ነው። የብሮድካስት ሥርጭትን በተመለከተ፣ የብሮድካስት ፍቃድ ባለቤት ግዴታ ከሆኑት መካከል በአንቀጽ 55/1/ረ፣ ከቀጥታ ሥርጭት ውጪ የማናቸውም ፕሮግራም ይዘት በጣቢያው ከመሰራጨቱ በፊት ሕግን የሚያከብር መሆኑን የማረጋገጥ የሚለው ድንጋጌ፤ አሁን በተሻሻለው ዐዋጅ የበለጠ ጠበቅ ብሎ፣ የማናቸውም ፕሮግራም ይዘት በጣቢያው ከመሰራጨቱ በፊት ወይም በሚሰራጭበት ጊዜ ሕግን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጥ በሚል ተሻሽሎ ተደንግጓል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ የዚህን ማሻሻያ መነሾ ሲያብራሩም፣ ቀጥታ ሥርጭት ስለሆነ ዜጎችን ከዜጎች የሚያጋጭ፣ አንዱን ሃይማኖት ከአንዱ ሃይማኖት ጋር የሚያጋጭ አድርጎ እንዲያቀርብ መደረግ የለበትም ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

ሳይነሳ የማይታለፈው የአዲሱ ዐዋጅ ማሻሻያ፣ የብሮድካስት አገልግሎት ሰጪዎችን የክፍያ ጉዳይ አስመልክቶ ያደረገው የአከፋፈል ማሻሻያ ነው። በዚህም፣ በቀደመው ዐዋጅ አንቀጽ 46/1 መሰረት፣ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ክፍያ ተፈጻሚ ከሆነ ለሬዲዮ ሞገድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ መክፈል እንደሚኖርበት በጥቅሉ ይደነግግ ነበር። በተሻሻለው ዐዋጅ መሠረት ግን፣ የፈቃድ ክፍያ እና ዓመታዊ የፈቃድ ማደሻ ክፍያን የሚቀበለው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ሲሆን፤ የራዲዮ ሞገድ ክፍያ ደግሞ የሚከፈለው ለኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን እንዲሆን ተደረጎነ ተሻሽሏል።

## የብሪጅ አጭር ምልከታ

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የሚመራው መንግስት ሊጠቀሱለት ከሚችሉ ተግባራት አንዱ፣ አፋኝ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ሕግጋትን ማሻሻሉ መሆኑ ግልጽ ነው። መንግስት ካሻሻላቸው ሕግጋት መካከል አንዱም፣ የአገሪቷን የመገናኛ ብዙኃን አስመልክቶ፣ በ2013 ዓ.ም. ያወጣው የመገናኛ ብዙኃን ዐዋጅ ቁጥር 1238 ነበር። ነገር ግን፣ ይኽ ዐዋጅ እንደቀደሙት መሰል ዐዋጆች ጥቂት ዓመታት ያህል እንኳን ሳያገለግል በወርኃ ሚያዚያ የመጀመሪያ ሳምንት እንዲሻሻል ሆኗል። የብሪጅ ቀዳሚ ነጥብም ይኸው የጊዜ ምጣኔ ጉዳይ ነው። ዐዋጁ ወደ ሥራ ከገባ ገና ኹለት ዓመቱ እንደሆነ ቢሆንም፣ ለመሻሻል የተፈለገው የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በቅጡ እንዳይከውን አድርጎታል በሚል ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ምክንያት ቀርቧል። ነገር ግን ዐዋጆች ሲወጡ፣ ረዘም ላሉ ጊዜያት እንዲያገለግሉ ታሳቢ ከመደረጋቸው ባለፈ፣ የሕግ ተገማችነት በየትኞቹም ዘርፎች ውስጥ እንዲኖርም ይኽ የጊዜ ምጣኔ ጉዳይ ወሳኝ መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ አሁን አገሪቷ ውስጥ ያሉት ግጭቶችም ሆኑ ቀጣዩ ብሔራዊ ምርጫ፣ ዐዋጁን ለማሻሻል በምክንያትነት ቢቀርቡም፣ ምርጫ ሲመጣ፣ የመናገር ነፃነት ምኅዳሩ እየታፈነ ሊሄድ ነውን? የሚለውን በቀደመው መንግስት ላይ ይቅረብ የነበረውን ትችት መልሶ እንዳያመጣው ያሰጋል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ዐዋጁ በዚህ መልኩ በፍጥነት ለማሻሻል የወሰነበትን ተሞክሮ በሌሎች ዐዋጆች ላይ ሊደግመው ከቻለ፣ መሠረታዊውን የሕግን ተገማችነት መርህ ጥያቄ ውስጥ ያስገባልና፣ ትምህርት ይወሰድበት የሚለው ቀዳሚው የተቋማችን ምክረ-ሐሳብ ነው።

በሌላ በኩል፣ ማሻሻያ ዐዋጁ ገና በረቂቅ ደረጃ ሳለ፣ ዐዋጁ ይመለከታቸዋል ከተባሉ ተቋማት እና የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ሰፊ የሚባል የአስረጂ መድረኮች መካሄዳቸው ይታወሳል፤ በእነዚያ መድረኮችም ላይ ከመገናኛ ብዙኃኑ ባለፈም፣ የተለያዩ ሀገር በቀል የመብት ተቆርቋሪዎች ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ የወጣው የ2013ቱ ዐዋጅ ባለበት እንዲቀጥል ሲጠይቁ መሰማቱ፣ ምናልባትም ያልተለመደ ሁነት ነበር። ብሪጅም፣ ከዚያ ካለተለመደ ዐዋጅ አይሻሻል የሚል ድምጽ ውስጥ፣ ቢያንስ በቀጣይ የዐዋጁ አተገባበር ላይ ሊወሰዱ የሚችሉ ሐሳቦች ሳይኖሩ አይቀሩምና ይታሰብበት ማለት ይፈልጋል።

ሌላይኛው ነጥብ፣ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን የቦርድ አባላት አወቃቀር የተመለከተው ማሻሻያ ነው። በአዲሱ ዐዋጅ መሰረት፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የቦርዱ አባላት መሆን የሚችሉበት አግባብ ተደንግጓል። እንደሚታወቀው ሚዲያ ያለውን የአራተኛ የመንግሥት አካልነት በአግባቡ እንዲወጣ፣ ከየትኞቹም የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ አመለካከቶች ገለልተኛ እንዲሆን ይጠበቃል። አሁን በተሻሻለው ዐዋጅ መሠረት፣ ፖለቲከኞች ወደዚያ ሚዲያ ተቆጣጣሪ ተቋም በቦርድ አባልነት እንዲካተቱ መወሰኑ፣ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን በፖለቲካ ሹመኞች ተጽዕኖ ሥር ሊጥለው የሚችልበት ዕድል ከመስፋቱ ባለፈ፤ በአንድ አልያም በተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፖለቲካ መስመሮች ምሪት፣ የትኛውም የመገናኛ ብዙኃን ፈቃዱ ሊቋረጥ አልያም መሰል ጫና ሊደረግበት የሚችልበትን ዕድል እንዳያበዛው ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልግ ይሆናል። በጥቅሉም፣ ብዙ ትችቶችን ያስተናገደው የተሻሻለው ዐዋጅ የሚዲያ ምኅዳሩን የማጥበብ፣ የተጀመረውን የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ የመቀልበስ እና የሰብዓዊ መብት ነፃነቶችንም የማደናቀፍ ሂደቶች ውስጥ እንዳይገባ፣ በተለይም የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብርቱ ቁጥጥር ያደርግ ዘንድ ማሳሰብ እንሻለን።



# እንደራሴ አልባዎቹ ወንበሮች እና እንድምታዎቻቸው

በአገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት ምርጫ ያልተካሄደባቸው ቦታዎች እንደመኖራቸው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 70 አካባቢ የሚሆኑ የእንደራሴዎች መቀመጫዎች ክፍት ሆነው አንድ የምርጫ ዘመንን እያገባደዱ ይገኛሉ። እነዚህ ክፍት መቀመጫዎች የተለያዩ አካባቢዎችን የሚወክሉ ቢሆንም፣ በተለይም የትግራይ ብሔራዊ ክልል ሙሉ በሙሉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያልተወከለ ሆኖ እናገኘዋለን። ምንም እንኳን የተወካዮች ምክር ቤት መንግስትን ለመመስረት የሚያስችል የድምጽ መጠን ቢያገኝም በትግራይ እና በሌሎች አካባቢዎች ምርጫዎች ባለመካሄዳቸው እና ያልተያዙ የውክልና ቦታዎች በመኖራቸው ቅቡልነቱ እና አካታችነቱ ጥያቄ ውስጥ የገባ እንዲሆን አድርጎታል።

ከዚህ አኳያም፣ በሕግ አወጣጥ ወቅት በተወካዮች አማካኝነት የሚንፀባረቁት የተለያዩ ሕዝቦች ፍላጎቶች በሚገባ ወይም ሙሉ በሙሉ አለመገለፃቸው እና አለመንፀባረቃቸው የቅቡልነቱ ሸንቁር ማሳያ አንዱ ገፅታ ነው። የማንነት እና የአመለካከት ልዩነቶችን አቃፊ እንዲሆን እና ራስን በራስ የማሥተዳደር ማረጋገጫ እንዲሆን ተደርጌ የተነደፈው ሕገ-መንግሥታዊ የፌደራል ሥርዓትም፣ በእነዚያ አካባቢ ሕዝቦች አለመወከል የተነሳ የማያደመጡ ድምጾች ያሉበት የተሸረፈ ሥርዓት እንዲሆን አድርጌታል ብለን እናምናለን። በመሆኑም ይህ የብሪጅ አጭር ምልከታ፣ ያለመወከል ሸንቁር የሚያስከትለውን ጣጣ እና መፍትሔዎቹን ለመዳሰስ ይሞክራል።

## ምን አጣን?

በሕግ አውጪ ምክር ቤት ውስጥ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ያለመወከል የመጀመሪያው መዘዝ፣ የመራጮችን/ የዜጎችን ጥቅም እና ፍላጎት ማስከበር የሚቻልባቸው የፖለቲካ ተሳትፎ እና የውክልና መርሆዎች ተግባራዊ አለመሆንን ማስከተሉ ነው። በፖለቲካ ፍልስፍናው የሚታወቀው ጆን ሎክ እንደሚያስረዳው፣ ማኅበራዊ ውል የሚመነጨው በመራጮች ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቅቡልነት ያለው አሥተዳደር ሲመሰረት ነው። ዜጎች በሕግ አወጣጥ ሂደት በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ድምፃቸው ከተነፈገ አልያም በወካዮቻቸው በኩል ማሰማት ካልቻሉ የተጓደለ ማኅበራዊ ውልይከተላል። ራስን በራስ ማሥተዳደር እና የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የተረጋገጡ ሆነው ሳለ፣ በትግራይ ክልል እና በሌሎች ምርጫ ባልተካሄዱባቸው ቦታዎች፣ ሕገ-መንግሥታዊው

> *ይህ ያለመወከል ጣጣ ካመጣቸው ሽንቁሮች ሌላው የትግራይም ሆኑ የሌሎች ውስን አካባቢዎች ምክር ቤቱ ባደረገው የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምስረታ እና በቀጣይ ሂደቶች ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ማደነቃቀፉ ነው።*

የዜጎች የመምረጥ እና የመመረጥ መብቶች ተግባራዊ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ይህ በተግባር የታየው ድምፅ አልባነት ዜጎች የመወከል፣ ፍላጎትን እና አመለካከትን የመግለጽ ዕድሎቻቸውን ነፍጓቸዋል። ይህም ፖለቲካዊ የመገለል ስሜትን ከመፍጠሩም ባሻገር፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት በሚፈጠረው አንፃራዊ የፖለቲካ መብቶች እጦትን ተከትሎ፣ ሁነቱ ወደባሰ ፖለቲካዊ ቀውስ እንዳያመራ ትኩረት ያሻዋል።

በአካታች እና በተረጋጋ የፖለቲካ ተቋሞች ጥናታዊ ሥራው የሚታወቀው ዶናልድ ሆሮዊትዝ እንደሚያትተው፣ የቡድኖችን ግጭቶች ወይም ማኅበራዊ ቀውሶችን መቀነስ የሚቻለው ተቋማዊ አካታችነትን ተግባራዊ በማድረግ ብቻ ነው። በትግራይ በተፈጠረው ቀውስ ምክንያት በተወካዮች ምክር ቤት የታየው ክፍተትም፣ ሕገ-መንግሥታዊ ማኅበራዊ ውሉን በመሸንቆር በፌዴራል መንግሥት ተቋማቶች እና በትግራይ አደረጃጀቶች መካከል አለመተማመንን እንዲስፋፋ ማድረግ ነው።

ምንም እንኳን አኹናዊው እና ሕገ-መንግሥታዊው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሂደት አብዛኛውን ድምፅ በማግኘት እየተፈፀመ ቢሆንም፣ ሙሉ በሙሉ የሆነ ሕዝባዊ ቅቡልነትን የተጎናጸፈ ነው ለማለት የሚያስደፍር አይሆንም። አብዛኛውን ድምፅ በማግኘት የሚፀድቁ ሕጐች ሕጋዊነታቸው አያጠራጥርም። ነገር ግን በትግራይ እና በሌሎችም የተወሰኑ አካባቢዎች በተነሱ ግጭቶች የተነሳ የጎደሉ ወንበሮች እና ውክልናዎች መኖር የሕግ አወጣጥን ሕጋዊነት ባያጠይቁትም ቅቡልነቱን ግን ሸንቁረውታል ብለን እናምናለን። ቅቡልነት የሕጋዊነት እና የሁሉን አሳታፊነት ውጤት ከመሆኑ አኳያ፣ ከሕጋዊነት የሚልቅ እና በተለይ በፌዴራላዊ አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ ዓይነተኛ ፖለቲካዊ ሚና እንዳለው ማስታወስ ያሻል።

ሌላይኛው የዚህ ሽንቁር ቅቡልነት ማሳያው፣ ምርጫ ያልተደረገባቸው አካባቢዎች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሥራ አስፈፃሚውን አካል የመቆጣጠር እንዲሁም በፖርላማ ክርክሮች እና የቁጥጥር ኮሚቴዎች ውስጥ አለመሳተፍን ማስከተሉ ነው። በፌዴራል አወቃቀር የሚገኙ ፓርላማዎች አሥፈፃሚውን አካል የመቆጣጠር ሥራቸው ሁሉን አቀፍ መሆን አለበት። በተለይም በፖርላማ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮች ያልተወከሉ አካባቢዎችን የሚዳስሱ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ችግሩን ያጐላዋል። ይህም የዴሞክራሲ ሂደቱን እምነት እንዳያድርበት ያድርገዋል። ያልተፈቱ ቅራኔዎች እንዲባባሱ፣ እንዲራዘሙ እና እርቅንም የሚያርቅ ስሜት ሊፈጥር ከመቻሉ ባለፈ፣ ዘላቂ ሰላምን እና ልማትንም ሊጎዳ ይችላል። ለዚህ ነጣላ ማሳያ የሚሆነን፣ እንደራሴዎቹ በሌሎቹ አካባቢዎች እንደሚያደርጉት በትግራይ ክልል እንዳችም የተቋማትም ሆነ የመስክ ጉብኝቶችን ማድረግ እንዳይችሉ መሆኑ ነው። ይህም፣ በዚያ ክልል ውስጥ ያሉት ዜጎች ስለ ሚያሳስቧቸው ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ድምጻቸውን እንዳያሰሙ፣ ችግሮቻቸውንም ሌላው የአገሪቷ ሕዝብ እንዳይረዳው ከማድረጉ ባለፈ፣ እንደራሴዎቹ ሕግጋት ሲያወጡ ቢያንስ የዚያን ክልል ሕዝብ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ እንዳይከቱ ማደረጉ ጭምር ነው። በተለይም፣ በሌሎች ክልሎች (ለምሳሌ ጋምቤላ) ያሉ የመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮች እና ስደተኞችን ምክር ቤቱ በውጪ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው በኩል ተመልክቶ መፍትሔ የሚበጅበትን መላ ሲያፈላልግ፣ ብዙ ተፈናቃይ ያለባትን ትግራይ ግን ምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለች መረዳት እንዳይችል ማድረጉንም ማንሳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ትግራይን በቀጥታ የነካው የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ሲወጣ፣ የትግራይ ክልል ተወካዮች አለመኖር ቢያንስ በሕጉ አተገባብር ላይ ጥላውን ማጥላቱ ግልጽ ሆኖ የወጣ ጉዳይ ይመስለናል።

ይህ ያለመወከል ጣጣ ካመጣቸው ሽንቁሮች ሌላው፣ የትግራይም ሆኑ የሌሎች ውስን አካባቢዎች  በምክር ቤቱ ባደረገው የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምስረታ እና በቀጣይ ሂደቶች ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ማደነቃቀፉ ነው።። ግጭትን በውይይት ወደ ሰላማዊ መንገድ መለወጥ በሚለው ሥራው የምናውቀው ጆን ፖል ሊደራሽ እንደሚያስገነዝበው፣ እውነተኛ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ እና ትምምን የሰፈነበት ብሔራዊ ውይይት ከሌለ እና በግጭት ውስጥ የነበሩትን ሁሉንም ኃይሎች የሚያካትት ብሔራዊ ምክክር ካልተካሄደ ዘላቂ ሰላም እና እርቅ ሳንካ ሊገጥማቸው ይችላል። ሊደራሽ ይህንን ሐሳብ ለማጠናከር ኢራቅን በምሳሌነት ሲያነሳ፣ ውስብስብ ግጭት ያለባቸው አገሮች ሁሉን አቀፍ ውይይት ባለመኖሩ ወይም ቁልፍ አካላትን ሳያካትቱ በመቅረታቸው ዘላቂ ሰላም እንዳይመጣ የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች በመዳሰስ ነው። በመሆኑም፣ ያለ እውነተኛ ተሳትፎ እና የመተማመን መንፈስ፣ ሰላም ሳንካ ሊገጥመው ይችላል የሚለው ማስጠንቀቂያው፣ መሰረታዊ ችግሮች ካልተፈቱ ግጭት እንደገና ሊቀሰቀስ እንደሚችል ያመለክታል። እርቅ ከፖለቲካ ስምምነት ይልቅ በሕዝቦች መካከል ያለ ጥልቅ ግንኙነትን እና ታሪካዊ ቁሬታዎችን በመዳሰስ ማኅበራዊ ፈውስን የማስገኘት ሂደት መሆኑንም ጸሓፊው ያሰምርበታል። : የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ው ፓርላማ ወሳኝ ፌደራላዊ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የሚያወጣቸው ሕጐች ለፖሊሲ አፈፃፀም ወሳኝ መሆናቸው እውን ነው። ፓርላማው ሕወሓትን ከሽብርተኝነት ዝርዝር ውስጥ ሲሰርዘው ለእርቅ እና ለፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ተግባራዊነት የራሱን ሚና ለመጫወት እንደፈለገ አመላካች መሆኑ ታይቷል። ነገር ግን ሕወሓት በጊዜያዊ አሥተዳደሩ ውስጥ የሚኖረው ሚና በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሠረት ተሰፍሮ ከተሰጠው በላይ በሚሆንበት ጊዜ፣ የፌዴራል መንግሥቱ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ተፅዕኖውን ባለማሳረፉ ምክንያት ተጨማሪ ሕግ እና ተጨማሪ የጊዜያዊ አሥተዳደር ቆይታ እንዲታወጅ ሆኗል። ይህም የሚያመለክተው ትግራይ እና ሌሎች

ያልተወከሉ አካባቢዎች በተወካዮች ምክር ቤት ያላቸው ሚና ወደ ዜሮ የተጠጋ በመሆኑ ለብሔራዊ አርቅ ሳንካ ሊሆን መቻሉ ነው። ከተለያዩ መረጃዎች እንደምንመለከተው፣ መንግሥት በብዙ ልፋት እና ጉልበት እየሄደበት ካለበት አገራዊ የምክክር ኮሚሽን፣ ከሕጋዊነቱ የተሰረዘው ሕወሓትም ሆነ ሌሎች የትግራይ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ በአንሳተፍም ባይነታቸው መቀጠላቸው ነው። ይህም፣ ከላይ እንደጠቀስነው፣ የውክልና ዕጦቱ ምን ያህል ለብሔራዊ ዕርቅ እና ምክክር ዕግዳት መሆኑን ነው።

በዚህ ሀተታ በመጨረሻ ሊነሳ የሚገባው በፓርላማ ውስጥ የሚገኙ ክፍት የተወካዮች መቀመጫዎች ፌዴራሊዝምን እና አንድነትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ መሆናቸውን ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም በብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መርሆዎች ላይ የመሰረተ መሆኑ እሙን ነው። የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎችም የተፈጠረውን ክፍተት በመጠቀም ቅሬታዎች እና የመገለል ስሜቶችን ሊያጦዙ ይችላሉ። በትግራይ ማሳያነት ለመጥቀስም፣ የውክልና ዕጦቱ፣ ትግራይ በፌዴሬሽኑ ውስጥ አልተወከለችም፣ በዚህ የተነሳም ከፌዴራል ሥርዓቱ መነጠል አለብን የሚሉ ድምጾች በአደባባይ ጭምር እንዲሰሙ መገፋፋቱ ነው። ይህ የመነጠል ስሜትም፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ሕግጋት አለመቀበልን ከማስከተሉ ባለፈ፣ ምክር ቤቱ በበጎ ዐይን አይመለከተንም የሚል አሉታዊ ስሜትን በማጎንጎን፣ ለከፋ ፖለቲካዊ ቀውሶች የተበራቱ የፖለቲካ ኃይሎች ድጋፍ ማግኚያ ማኅበራዊ መሰረትን ማመቻቸቱ አሌ የሚባል አይደለም።

ይህም የፌዴራሉን የማኅበራዊ ውል ከማላላቱም ባሻገር የረጅም ጊዜ ያለመረጋጋት ምንጭም ሊሆን ስለሚችል፣ በቀጣዩ ምርጫ አንድም ክፍት የተከወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ እንዳይኖር በትኩረት ሊሰራበት ይገባል እንላለን። በፓርላማ ውስጥ የሕዝዝቦችን ድርሻ ማረጋገጥ የዴሞክራሲ መርህ ብቻ ሳይሆን የአገራዊ መረጋጋት እና አንድነትን ማረጋገጫ ማሳተም ነውና።

## ምክረ-ሐሳቦች

በፓርላማ ውስጥ አለመወከል የሚፈጥሩትን ደፋዎች ለመቅረፍ ብሪጅ የሚከተሉትን ምክረ-ሐሳቦች ያቀርባል።

- በትግራይ ክልልም ሆነ በሌሎች ውስን ቦታዎች ምርጫ እንዲካሄድ የማያስችሉ የፀጥታ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እንዲቀረፉ በማድረግ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ አሁን ያለውን ሕጋዊ ሂደት ወደ ሙሉ ቅቡልነት በማሸጋገር ከፍ ወዳለ ሰላም እና ልማት የሚደረገውን ጉዞ ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ለአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን የተፈጠረውን ይህንን ሽንቁር ለመድፈን አሁንም የጊዜያዊ አሥተዳደሩ ጊዜ ከዚህ በላይ እንዳይራዘም አስፈላጊውን ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ተገቢ ነው። ምርጫ ባልተካሄደባቸው ቦታዎች ሁሉ በሰባተኛው ብሔራዊ የምርጫ እቅድ ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ አካታችነትን፣ አሳታፊነትን እና ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ሁነኛ መፍትሔ ነው እንላለን።
- ፓርላማው የብሔራዊ የምክክር ኮሚሽኑ አሁን በደረሰበት ደረጃ የትግራይ ክልል ነዋሪዎች በሂደቱ የሚካተቱበትን መንገድ እንዲያመቻች እና እንዲተገብር ግፊት ማድረግ ይኖርበታል። እስካሁን በዋነኝነት ከተሰሩት ሥራዎች መካከል የአጀንዳ ልየታ አንዱና ዋነኛው በመሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች ድምጽ ቢያንስ በጊዜያዊ አሥተዳደሩ አማካኝነት ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ ኮሚሽኑ የተሰጠውን ኃላፊነት እንዲወጣ ማመቻቸት ተገቢ መሆኑን አበክረን መጥቀስ እንሻለን።
- በመጨረሻም በትግራይ ክልልም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ሕዝቦች በተወካዮች ምክር ቤት አለመወከላቸው፣ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ የቴክኒክ ጉዳዮች አለመሟላት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ በአገሪቱ መረጋጋት፣ የረጅም ጊዜ እድገት እና ዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ፣ ሁሉም የሚመለከተው አካል የውክልና ዴሞክራሲ ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋገጥ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል እንላለን።

እንደራሴ

እንደራሴ በብረጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.